# ግንኙነት

## ሕይወትን በክርስቶስ ላይ መመስረት



# ግንኙነት

## ሕይወትን በክርስቶስ ላይ መመስረት



# ግንኙነት

## ሕይወትን በክርስቶስ ላይ መመስረት

## ፖል ጎትሃርድት

ትርጉም፥ ተመስገን ሳህለ

አርትዖት፥ ዘላለም መንግሥቱ

በተለየ ሁኔታ ካተገለጸ በስተቀር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ሁሉ የተጠቀሱት
በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኀበር ከታተመው የ1954 ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

Copyright © 2012 by *Life Baptist Church* in Las Vegas

# እንኳን ደስ ያላችሁ!

ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ እንኳን በደህና መጣችሁ። ከክርስቶስ ጋር ይህንን ግንኙነት ስትጀምሩ እርሱን እንድትከተሉ የሚያግዟችሁን አንዳንድ መርጃዎች ማቅረብ እንሻለን።

በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነታችሁን በማድረግ ስትመለሱ እንደ ክርስቲያን አዲስ ሕይወትን ትጀምራላችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን አዲስ ሕይወት ለመግለጥ በርካታ ቃላትና ሐረጎች ይጠቀማል። ለምሳሌ፥ እናንተ፥ 'ተዋጅታችኋል፥' 'ዳግም ተወልዳችኋል፥' 'የእግዚአብሔር ልጆች ሆናችኋል፥' 'የእግዚአብሔር ወዳጆች ሆናችኋል፥' 'በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ሆናችኋል፥' ሌላም ብዙ ይላችኋል። በአጭር ቃል፥ በቃሉ መሠረት በክርስቶስ አዲስ ማንነትን አግኝታችኋል።

እንደ ክርስቲያን የሚኖራችሁ እድገት ዋና አካል ይህንን በክርስቶስ የሆነውን ማንነት መረዳት እና ማጽናት ነው። ብሎም ክርስትና እናንተ ለራሳችሁ ሳይሆን ለእግዚአብሔር መኖራችሁ እንዳሆነ ትረዳላችሁ። ክርስትና እግዚአብሔር የራሱን ሕይወት በእናንተ መኖሩ ነው። ይህ ሕይወት በክርስቶስ ያላችሁን ማንነት ስትረዱት እና ከእርሱ ጋር ያላችሁን ግንኙነት በመፈለግ ስትቀጥሉ እውን ይሆናል። በሚቀጥሉት ሰባት ቀናት የትምህርት ክፍለ ጊዜ ይህ መጽሐፍ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ እንድታገኙ ያግዛችኋል፥

1ኛ ቀን፥ በክርስቶስ ያገኘሁት አዲስ ሕይወት ምንድን ነው?

2ኛ ቀን፥ የዘላለም ሕይወት ማለት ምን ማለት ነው?

3ኛ ቀን፥ የክርስቲያን ሕይወት ግብ ምንድን ነው?

4ኛ ቀን፥ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ምን ማለት ነው?

5ኛ ቀን፥ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ላጠና እችላለሁ?


6ኛ ቀን፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን በተከታታይ ለምን እሄዳለሁ?

7ኛ ቀን፥ እንደ ክርስቲያን ለማደግ ምን ማድረግ አለብኝ?

ሮሜ. 8፥29፥ ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኵር ይሆን ዘንድ፥ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና፥ ይላል።

እግዚአብሔር ባሕርያችሁን ከክርስቶስ ባሕርይ ጋር ሊያመሳስለው ይፈልጋል። እንደ ክርስቲያን በአእምሮአችሁ እና በእድገታችሁ እንድትጎለብቱ ይፈልጋል። የዚህ መጽሐፍ ግብ በትክክለኛው መንገድ እንድትሄዱ ማገዝ ነው።

የክርስቶስን ሕይወት እያወቃችሁ በምትሄዱበት ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።



# ይህችን መጽሐፊት እንዴት መጠቀም ይቻላል?

1. መጽሐፍ ቅዱስ፥ እስክሪብቶ እና ማድመቂያ ያስፈልጋችኋል።
2. መረጃውን በጥንቃቄ አንብቡ፥ ከዚያም እየቀጠላችሁ ስትሄዱ ክፍት ቦታዎቹን በሙሉ መልሱ።
3. ከተቻለ ክርስቲያን እንደሆናችሁ ወዲያውኑ ይህንን ማስታወሻ ለማጥናት ሞክሩ። ካመናችሁ የቆያችሁ ከሆነ ይህንን መጽሐፍ በትክክለኛ መንገድ ላይ መሆናችሁን ለማረጋገጥ እንደ መርጃ መምሪያ ተጠቀሙበት።
4. እግዚአብሔር ዕድሎችን በፈጠረላችሁ መጠን እነዚህን ትምህርቶች ለሌሎች አካፍሉ።

## 1ኛ ቀን፥ በክርስቶስ ያገኘሁት አዲስ ማንነት ምንድን ነው?

ማንነታችንን እኛን ይገልጸናል። ማንነታችን በአብዛኛው ከምናደርገው፥ ከምንወደው፥ ከተገኘንበት ስፍራ፥ ወይም እራሳችንን ከምንመለከትበት እውነታ ጋር የተያያዘ ነው። ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ እራሳቸውን ምን ብለው እንደሚስተዋውቁ ልብ በሉ። "እንደምን አደራችሁ፤ ስሜ ዶ/ር አስቻለው ነው፤ የሕጻናት ሃኪም ነኝ።" "ሰላም፥ እኔ ረዳ ነኝ፤ የሰባተኛ ክፍል ታሪክ አስተምራለሁ።" "እንዴት ናችሁ? ስሜ ማይክ ነው። የመጠጥ ሱሰኛ ነኝ።" ማንነታችን እኛን ይገልጸናል።

ከክርስቶስ በፊት ማንነታችን ከዚህ ቀደም ባደረግነው ይገለጻል። ሮሜ 3፡23 ይህን ይነግረናል። "ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል።" ጥቂትም ሆነ ብዙ ኃጢአት መሥራታችን ምንም ለውጥ የለውም፤ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋል፤ እናም ሁሉም ሁሉም ኃጢአተኛ ተብለው ተገልጸዋል።

በክርስቶስ ላይ እምነታችን በማድረግ ከኃጢአታችሁ ስትመለሱ አዲስ ማንነት ተሰጥቶአችኋል። ከዚህ በኋላ በኃጢአታችሁ አትገለጹም፥ የምትገለጹት በክርስቶስ ጽድቅ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በገላ. 2፡20 "ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፥ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፥ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው።" ብሏል። ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ይኖራል።

ዊሊያም ከልበርትሰን ይህንን ለውጥ (ክርስቶስ ሲያድናችሁ እና የራሱን ማንነት ሲሰጣችሁ የሚለውን) በሮሜ 6፡6-8 መሠረት እንዲህ ብለው ይገልጹታል። "በመስቀል ላይ የሞተው ማን ነው? በእርግጥ የተባረከው ጌታችን ነው በመስቀል ላይ የሞተው። ግን ሌላ የሞተ የለም? ማን? ቃሉ ይህን ይላል፤ ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፥ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና። ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንድንኖር እናምናለን።"

አንደ ክርስቲያን አዲሱ ማንነታችሁ በክርስቶስ የተገኘ ነው። እርሱ በመስቀሉ ላይ በሞተ ጊዜ እናተም በመስቀል ላይ ሞታችኋል፤ (ሮሜ 6፡6-8) ከሞት በተነሣ ጊዜ እናንተም ከሞት ተነስታችኋል፤ (ቆላስይስ 2፡12)። እናንተ በክርስቶስ ናችሁ ክርስቶስም በእናንተ። እርሱ የእናንተ ማንነት ነው!

ያ ማለት ከክርስቶስ ጋር እኩል ሆናችኋል ማለት አይደለም። በቀላሉ የድሮ ሕይወታችሁ አልፏል ማለት ነው። አዲሱ ሕይወታችሁም በክርስቶስ ተገኝቷል፤ (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17)።

በሚቀጥለው ገጽ ያለው ሰንጠረዥ ከእግዚአብሔር አንጻር ያለውን አዲሱን ማንነታችሁን ይዘረዝራል።

# እናንተ ማን ናችሁ?

እናንተ የምድር ጨው ናችሁ። (ማቴ. 5፥13)
እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። (ማቴ. 5፥14)
የእግዚአብሔር ልጅ (የቤተሰቡ አባል) ናችሁ። (ዮሐ. 1፥12፥ ሮሜ 8፥16)
የእውነተኛው የወይን ግንድ አካል ናችሁ። (ዮሐ. 15፥1, 5)
የክርስቶስ ወዳጆች ናችሁ። (ዮሐ. 15፥15)
የእርሱን ፍሬ እንድታፈሩ በክርስቶስ የተመረጣችሁ እና የተሾማችሁ ናችሁ። (ዮሐ. 15፥16)
የክርስቶስ ግላዊ ምስክሮች ናችሁ። (ሐዋ. 1፥8)
የጽድቅ ባሪያ ናችሁ። (ሮሜ 6፥18)
የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆናችኋል። (ሮሜ 6፥22)
የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ። (ሮሜ 8፥14, 15፥ ገላ. 3፥26፥ 4፥6)
ከክርስቶስ ጋር አብሮ ወራሾች ናችሁ። (ሮሜ 8፥17)
የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ናችሁ። (1ኛ ቆሮ. 3፥16፥ 6፥19)
ከጌታ ጋር ተባብራችኋል እናም ከእርሱ ጋር አንድ መንፈስ ሆናችኋል። (1ኛ ቆሮ. 6፥17)
የክርስቶስ አካል ብልት ናችሁ። (1ኛ ቆሮ. 12፥27፥ ኤፌ. 5፥30)
አዲስ ፍጥረት ናችሁ። (2ኛ ቆሮ. 5፥17)
ከእግዚአብሔር ጋር ታርቃችኋል፥ የእርቅ አገልጋዮችም ናችሁ። (2ኛ ቆሮ. 5፥18–19)
የእግዚአብሔር ልጅ ናችሁ እናም በክርስቶስ አንድ ናችሁ። (ገላ. 3፥26–28)
የእግዚአብሔር ወራሽ ናችሁ። (ገላ. 4፥6–7)
ቅዱስ ናችሁ። (ኤፌ. 1፥1፥ 1ኛ ቆሮ. 1፥2፥ ፊል. 1፥1፥ ቆላ. 1፥2)
የእግዚአብሔር ፍጥረቱ ናችሁ። (ኤፌ. 2፥10)
በእርሱ ቤተሰብ ውስጥ የተወደዳችሁ ዜጎች ናችሁ። (ኤፌ. 2፥19)
የክርስቶስ እስረኞች ናችሁ። (ኤፌ. 3፥1፥ 4፥1)
ጻድቃን እና ቅዱሳን ናችሁ። (ኤፌ. 4፥24)
የመንግሥተ ሰማያት ዜጎች እና አሁንም በመንግሥተ ሰማይ የተቀመጣችሁ ናችሁ። (ፊል. 3፥20፥ ኤፌ. 2፥6)
ከክርስቶስ ጋር በእግዚአብሔር ተሰውራችኋል። (ቆላ. 3፥3)
የክርስቶስ ሕይወት መገለጫ ናችሁ። (ቆላስይስ 3፥4)
የእግዚአብሔር ምርጦች፥ ቅዱሳን እና የተወደዳችሁ ናችሁ። (ቆላ. 3፥12)
በእግዚአብሔር ተመርጣችኋል እናም ተወዳችኋል። (1ኛ ተሰ. 1፥4)
የብርሃን ልጆች ናችሁ እንጂ ከጨለማ አይደላችሁም። (1ኛ ተሰ. 5፥5)
ቅዱሳን ወንድሞችና የሰማያዊ ጥሪ ተካፋዮች ናችሁ። (ዕብ. 3፥1)
የክርስቶስ ተካፋዮች ናችሁ። (ዕብ. 3፥14)
ሕያዋን ድንጋዮች ናችሁ። (1ኛ ጴጥ. 2፥5)
የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ ናችሁ። (1ኛ ጴጥ. 2፥9–10)
ለዚህች ዓለም ያልታወቃችሁ መጻተኞች እና እንግዶች ናችሁ። (1ኛ ጴጥ. 2፥11)
የሰይጣን ጠላቶች ናችሁ። (1ጴጥ. 5፥8)
የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ። (1ኛ ዮሐ. 3፥1–2)
ከእግዚአብሔር የተወለዳችሁ ናችሁ እናም ክፉው (ዲያብሎስ) ሊነካችሁ አይችልም። (1ኛ ዮሐ. 5፥18)
የማስማሪያው በጎቹ ናችሁ። (መዝ. 23 እና 100)

**የክርስትና ሕይወት ዋናው ክፍል እራሳችሁን ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር መመልከት መጀመር ነው። ስለራሳችሁ የበለጠ የሚናገሩትን ልታሰምሩባቸው ጥቂት ጊዜ ውሰዱ።**

## 2ኛ ቀን፥ የዘላለም ሕይወት ምንድን ነው?

እንደ አንድ የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ የዘላለም ሕይወት ነጻ ስጦታ ተሰጥቷችኋል፤ (ሮሜ 6፡23)። ያ ታላቅ ዜና ነው። እንደ አለመታደል ሆኖ በርካታ ክርስቲያኖች ስለ ዘላለም ሕይወት ግራ የተጋቡ ናቸው። የዘላለም ሕይወትን ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር ለመግለጽ ጠቂት ጊዜ እንውሰድ።

ኢየሱስ ስለ ዘላለም ሕይወት በተደጋጋሚ ተናግሯል። እንዲህ ብሏል፥

- "በእርሱ የሚያምን ሁሉ **የዘላለም ሕይወት** እንዲኖረው . . ." (ዮሐ. 3፥15)
- "ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ **የዘላለም ሕይወትን** እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፤" (ዮሐ. 6፥40)
- "በእርሱ የሚያምን ሁሉ **የዘላለም ሕይወት** እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።" (ዮሐ. 3፥16)
- "እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ **ለዘላለም ሕይወት** የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ።" (ዮሐ. 4፥14)

ኢየሱስ በሄደበት ስፍራ ሁሉ ስለ ዘላለማዊው ሕይወት ተናግሯል። በመልእክቶቹ አንስቶታል፥ ወደ አባቱም ጸልዮታል ደግሞም ለደቀ መዛሙርቱ አስተምሮታል። በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት በክርስቶስ ያመኑ የዘላለም ሕይወት እንደሚኖራቸው እናውቃለን። ነገር ግን የዘላለም ሕይወት ማለት ምን ማለት ነው? በዮሐ. 17 ኢየሱስ በተግባር እስኪገልጸው ድረስ አልተገለጸም ነበር።

- "እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።" (ዮሐ. 17፥3)

የዘላለም ሕይወት አግዚአብሔርን ማወቅ ነው። ክርስቶስ የመንግሥተ ሰማያት ክብርን ወደ ጎን ትቶ ወደ ምድር የመጣበት ምክንያት እኛ አግዚአብሔርን እንድናውቅ ነው። በርካታ ክርስቲያኖች በስሕተት የዘላለም ሕይወት ስትሞቱ ወደ መንግሥተ ሰማይ መሄድ ነው ብለው ይገምታሉ። መንግሥተ ሰማይ ታላቅ ነው። ነገር ግን ወደ መንግሥተ ሰማያት መሄድ እግዚአብሔርን የማወቅ ውጤት ነው፥ ዋናው ስጦታ ግን አይደለም።

የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ስጦታ እርሱ እራሱ ነው። እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት እንዲኖን ነበር የተፈጠርነው፥ ኃጢአት ያንን ግንኙነት አለያየው። ኢየሱስ ግንኙነቱን ለማስታረቅ ሞተ፤ እና እንደገና ተነሳ። የዘላለም ሕይወት አግዚአብሔርን በግላዊ ግንኙነት ማወቅ ነው።

የዘላለም ሕይወት ማለት አግዚአብሔርን ማወቅ ከሆነ እንዴት እርሱን ወደ ማወቅ ልንደርስ እንችላለን?

በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር እራሱን ሊገልጥ ይገባል።

ሁለተኛ፥ እርሱ የገለጠውን እኛ ልናምን ይገባል።

ሦስተኛ፥ ከተገለጠው ጋር ጊዜ ልናሳልፍ ይገባል።

እግዚአብሔር እራሱን እንዴት ገልጿል? እራሱን በሚከተሉት ውስጥ ገልጿል።...

- በተፈጥሮ (መዝ. 19፥1–4፥ (ሮሜ. 1፥20)
- በሕሊና (ሮሜ. 2፥14–15)
- በክርስቶስ (ዮሐ. 1፥1፥ 5፥18፥ 8፥58፥ 14፥9፥ ዕብ. 1፥1–2)
- በቅዱስ ቃሉ ቀኖና (ዮሐ. 20፥31፥ 2ኛ ጢሞ. 3፥16፥ 2ኛ ጴጥሮስ 1፥21)

እግዚአብሔር የገለጠውን ማመን ለምን ጠቃሚ ሆነ? እምነት ለወንጌሉ መልዕክት ማዕከላዊው ጉዳይ ነው። ቀደም ባለው ገጽ በቃሉ ውስጥ ካሉት ጥቅሶች እንዳየነው በክርስቶስ ላመኑ የዘላለም ሕይወት ተሰጥቷል። ይህም ማለት አንድ ሰው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እና በመስቀል እንደሞተ፥ ከሞትም እንደተነሣና የዘላለም ሕይወት እንደሚሰጥ ያምናል ማለት ነው። ክርስቶስ ማን መሆኑ እና ክርስቶስ በመስቀል ያደረገው ነገር የወንጌሉ ዋናው መልእክት ነው። ይህም በእምነት ሊቀበሉት (የታመነ ሊሆን) ይገባል።

በመጨረሻ፥ ከዚህ ከተገለጠው ጌታ ጋር የግድ ጊዜ ልናሳልፍ ይገባናል። አንድን ሰው ለማወቅ የሚያስችል ብቸኛው መንገድ ከዚያ ሰው ጋር ጊዜን ማሳለፍ ነው። ስለ አንድ ሰው ከመጽሐፍ ልትማሩ ትችላላችሁ፥ ነገር ግን ያንን ሰው በእርግጥ ልታውቁት የምትችሉት አብራችሁ ጊዜ ስታሳልፉ ነው። ከአንድ ሰው ጋር ስትሆኑ የእነርሱን ባህርያት፥ የሚወዱትን፥ የሚጠሉትን፥ ስሜታቸውን፥ ዝንባሌያቸውን፥ አመለካከታቸውን፥ ልባቸውን፥ የሚስቡበትን መንገድ እና እንዴት ምላሽ እንደሚሰጡ ያንን በቀላሉ ታውቃላችሁ ወይም ትወርሳላችሁ። አንድ ሰውን ከእርሱ ጋር ጊዜ በማሳለፍ ነው ልታውቁት የምትችሉት።

ከላይ ያየናቸውን ልዩ ልዩ ነገሮች አንድ ላይ እናድርጋቸው። የዘላለም ሕይወት እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። እግዚአብሔርን ልናውቅ የቻልነው ወይም የምንችለው ወይም የምናውቀው እርሱ ራሱን ለኛ ስለገለጠልን፥ እርሱ የገለጠውን በማመን እና ከእርሱ ጋር ጊዜ በማሳለፍ ነው።

ከላይ ያለውን ዮሐ. 15፥1-8ን ከመጽሐፍ ቅዱሳችሁ ተመልከቱ። ክርስቶስ ምን ያህል ጊዜ ነው በእርሱ እንድንኖር የተናገረው? በእርሱ መኖር ማለት ከእርሱ ጋር አብሮ መሆን፥ በእርሱ ዘንድ መቆየት፥ በእርሱ በቤቱ መገኘት ነው። ባነበባችሁት መሠረት በክርስቶስ መኖር ምን ያህል እግዚአብሔርን እንድታውቁ ይረዳችኋል?

እግዚአብሔር እራሱን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ገልጦአል። እርሱን የማወቅ አንዱ ክፍል እርሱ የገለጠውን ማመን ነው። ቆላ. 1፥15-19ን ተመልከቱ። በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ስለ ራሱ ምን ገልጦአል? በዚህ ክፍል የተጻፉትን በርካታ ዋና ዋና ባህርያቱን ጻፉ። እነዚህን ባህርያቱን አመናችሁን?

ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜን ስታሳልፉ እና የገለጠላችሁን ስታምኑ እርሱን ወደ ማወቅ ትደርሳላችሁ። እርሱን ወደ ማወቅ ስትደርሱም የዘላለም ሕይወትን ትማመዳላችሁ።

# 3ኛ ቀን፥ የክርስትና ሕይወት ግብ ምንድን ነው?

እግዚአብሔር ለሰው ዘር የሰጠው ስጦታ የዘላለም ሕይወት (እርሱን ማወቅ) ከሆነ እንግዲህ የኛም የመጨረሻ ግብ ያንን ስጦታ መቀበል ወይም ማቀፍ መሆን አለበት። ይህ ክፍል በተወሰነ መልኩ የትናንትናው ትምህርት ቀጣይ ነው። አሁን የዘላለም ሕይወትን መሠረት ከተረዳን የክርስቲያን ሕይወት ግብን አጥርተን መመልከት እንችላለን።

የክርስቲያን ሕይወት ግብ ምንድን ነው? ግቡ ባለ ሁለት ክፍል ነው።

## የመጨረሻ ዋና ግቡ አግዚአብሔርን ማወቅ ነው።

እኛ የዘላለም ሕይወት ስጦታን እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ በመድረስ እንጨብጣለን። ይህም በፍጥረት ጅማሬ ወደ ነበረን ዓላማ ይመልሰናል። እኛ የተፈጠርነው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ ነበር። ያም ወደ ሁለተኛው ግባችን ይወስደናል። አንድን ሰው በእውን ለማወቅ እንዴት ትችላላችሁ?

## ዕለታዊ ግባችን ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜን ማሳለፍ ነው።

ትናት እንዳየነው አንድን ሰው ወደ ማወቅ ልንደርስ የምንችልበት ብቸኛ መንገድ ከዚያ ሰው ጋር ጊዜ በማሳለፍ ነው። ስለ አንድ ሰው ከመጽሐፍ ልትማሩ ትችላላችሁ፥ ነገር ግን ያንን ሰው ወደ ማወቅ ልትደርሱ የምትችሉት ከእርሱ ጋር አብራችሁ ጊዜ በማሳለፍ ብቻ ነው። ይህንን ጽንሰ አሳብ በጥቂቱ ገለጥ አድርገን እንየው።

ስለ የፍቅረኞች የመጠናኛ አብሮ የማሳለፊያ ጊዜ ጥቂት አስቡ። አብሮ የማሳለፉ ተቀዳሚ ዓላማ ከአንድ ሰው ጋር መጣጣም መቻሉን ለማወቅ ነው። በአብሮ በማሳለፍ ጊዜ ወደሚሄዱበት ትሄዳላችሁ፥ የሚያደርጉትን ታደርጋላችሁ፥ ልባቸው ምን ላይ እንዳለ፥ ባህሪያቸውን፥ ሕልሞቻቸውን እና ዕቅዶቻቸውን ለመረዳት ትጥራላችሁ። አብራችሁ ጊዜ በማሳለፍ ማንነታቸውን፥ ስነምግባራቸውን ወዘተ፥ ታውቃላችሁ። በጊዜ ሂደት ግለሰቡን ወደ ማወቅ ትደርሳላችሁ።

አግዚአብሔርንም ለማወቅ ተመሳሳይ ስልት ተጠቀሙ። ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት ጊዜ ልታሳልፉ ትችላላችሁ? በቀጣዩ ገጽ አንዳንድ የተለመዱ መንገዶች ቀርበውላችኋል። እነዚህ አብዛኛዎቹ የክርስትና እምነት "ሥነ ምግባራት" ተብለው ይገለጣሉ።

• ***መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ የማሳለፊያ እና እርሱን ወደ ማወቅ የመድረሻ አቅጣጫ ነው።*** መጽሐፍ ቅዱስ አግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት መገለጥ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ባህርይውን፥ የልቡን አሳብ፥ መሻቱን፥ እና እቅዶቹን ገልጦአል። መጽሐፍ ቅዱስን የበለጠ ባጠናችሁ ቁጥር የተሻለ እግዚአብሔርን ታውቃላችሁ ብሎም ትርረዱታላችሁ።

• ***በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ የማሳለፊያ እና እርሱን ወደ ማወቅ የመድረሻ አቅጣጫ ነው።*** ጸሎት የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ለእግዚአብሔር መንገር ብቻ አይደለም። ጸሎት እግዚአብሔር ሲናገራችሁ መስማትም ነው። በጸሎት የእግዚአብሔር ድምጽ መለየት ጊዜ ይወስዳል። ይሁንና የበለጠ ከእርሱ ጋር ስትሆኑ የበለጠ ድምጹን ለይታችሁ እያወቃችሁ ትሄዳላችሁ።

• ***እግዚአብሔርን ማምለክ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ የማሳለፊያ እና እርሱን ወደ ማወቅ የመድረሻ አቅጣጫ ነው።*** አምልኮ መዘመር ብቻ አይደለም። አግዚአብሔርን በሕይወታችን፥ በውሳኔዎቻችን፥ በተግባሮቻችን እና በመሻታችን እናመልካለን። አምልኮ በጣም በቀላሉ አግዚአብሔር ስላደረገው ነገር ምስጋና የምናቀርብበት፥ ወይም በጊዜው ስለሚያነሣሳን ነገር መታዘዛችንን የምንገልጥበት፥ ወይም በእርሱ ላይ ያተኮረ ምላሽ ብቻ ሊሆን ይችላል።

• ***መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ስብከትን እና ትምህርትን መስማት ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ የማሳለፊያ እና እርሱን ወደ ማወቅ የመድረሻ አቅጣጫ ነው።*** 2ጢሞ. 2፥15 "የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።" ይላል። ማናቸውም ሰዎች በራሳቸው እግዚአብሔርን ለይተው ሊውቁት አይችሉም። ክርስትና ከሌሎች አማኞች ጋር መተባበርን ይጠይቃል። መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው ስብከት እና ትምህርት ስትሰሙ ያ ወደ ክርስቶስ ያመለክታችኋል፥ ክርስቶስን ያከብራል፥ በክርስቶስ የሆነ እምነትን ያበረታታል፥ የክርስቶስን ትምህርቶች ይካፈላል፥ ወዘተ። እንደዚህ ነገሮች ሁሉ እርሱን የበለጠ እንድታውቁት ያግዟችኋል።

• ***በተፈጥሮ ውስጥ ጊዜ ማሳለፍ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ የማሳለፊያ እና እርሱን ወደ ማወቅ የመድረሻ አቅጣጫ ሊሆን ይችላል።*** ሮሜ 1 የእግዚአብሔር የማይታዩ መገለጫዎች፥ ተፈጥሮ፥ እና ባህርይው በፈጠረው ፍጥረት በግልጽ እንደሚታዩ ይነገረናል። ዘማሪው ሰማያት በእግዚአብሔር ክብር ተሞልተዋል ብሎ ያውጃል። የእግዚአብሔር ልዩ መገለጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደሚኝ የእግዚአብሔር ጥቅል መገለጥ ደግሞ በተፈጥሮ ውስጥ ሊታይ ይችላል።

የትኛውንም ስልት ለመከተል መምረጣችሁ ሳይወስናችሁ፥ ግቡ ትኩረታችሁ በእርሱ ላይ እንደሆነ ከእርሱ ጋር ጊዜ ማሳለፋችሁ ነው።

እስኪ እንከልስ። የመጨረሻው ግብ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። ግቡ ስለ እግዚአብሔር ማወቅ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሄርን ራሱን ማወቅ ነው። ግቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑር ለመሆንም አይደለም። ግቡ እርሱን ማወቅ ነው። ለአንድ ሰው የሕይወት ዘመኑን/ኗን በእውን እግዚአብሔርን ወደ ማወቅ ሳይደርስ / ሳትደርስ ስለ እግዚአብሔር በመማር እና መንፈሳዊ ነገሮችን በማድረግ ብቻ ማሳለፍ ሊሆን የሚችል ነገር ነው።

ዕለታዊ ግቡ ከእርሱ ጋር ጊዜ ማሳፍ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ለመሆን እና እርሱን ወደ ማወቅ ለመድረስ መንገዶችን ልናገኝ ይገባል። በትምህርቱ ውስጥ የቀረቡትን አቅጣጫዎች ዝርዝር ከልሱ። የመጀመሪው ግብ ሕይወታችሁን ይመራል። ሁለተኛው ግብ ቀናችሁን (ዕለታዊ ኑሮአችሁን) ይመራል።

አንድ ክርስቲያን እነዚህን ሁለት ግቦች በአእምሮው የፊተኛ ስፍራ ሰጥቶ ከጠበቀ የክርስቶስን ሕይወት በመረዳት እና በመኖር ሂደት ታላቅ እርምጃዎችን ይወስዳሉ።

ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜን ማሳለፊያ መንገዶች (በዚህ ትምህርት በቀደመው ገጽ ውስጥ የሚገኙት ስነ ምግባራት) መሠረት ዛሬ ልትጀምሯቸው የምትችሏቸውን ልዩ ልዩ ነገሮች ዘርዝሩ።

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

______________________________________________________________________________

ግቡ የመጽሐፍ ቅዱሱን እግዚአብሔርን ለማወቅ ከሆነ ያንን ግብ ላማሳካት ማን ሊያግዛችሁ ይችላል? የተለያዩ በግልጽ የሚታወቁ ሰዎችን ወይም የሰዎች አይነቶችን ዘርዝሩ፥ ከዘረዘራችኋቸው መካከል ጥቂቱን አግኟቸው።

ተጨማሪ ማስታወሻዎች፤

## 4ኛ ቀን፥ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር መሆን ምን ማለት ነው?

*"ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው። ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ። እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፥ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"* (ማቴዎስ 28፥18–20)

በዚህ ጥቅስ ሊመለሱ የሚገባቸው ሁለት ጥያቄዎች ይነሣሉ። አንዱ፥ ደቀ መዝሙር ምንድን ነው? የሚለው ሲሆን ሁለተኛው፥ ደቀ መዛሙርት እንዴት ይሠራሉ? የሚል ነው።

ከአንደኛው ክፍለ ዘመን የአይሁድ እይታ በመነሣት ደቀ መዝሙር ማለት ልክ እንደ እርሱ ለመሆን ከአንድ መምህር ወይም ረቢ ጋር እርሱን በማድመጥ፥ በማየት፥ የእርሱን አካሄድ በመቅዳት ጊዜን የሚያሳልፉ፥ እና በመጨረሻም የእርሱን ትምህርት ለሌሎች የሚያስተላልፉ ናቸው።

በአዲስ ኪዳስ ኢየሱስ ብዙ ጊዜያት (ከ40 በላይ) 'መምህር ሆይ' ወይም በቋንቋቸው ረቢ እየተባለ ተጠርቷል። እርሱ የኛ ረቢ ነው እኛም የእርሱ ደቀ መዛሙርት ነን። እንደ ደቀ መዛሙርት ልክ እንደ እርሱ እንድንሆን እና በሂደት የእርሱን ትምህርቶች ለሌሎች እንድናስተላልፍ ከእርሱ ጋር (እርሱን በመስማት፥ እርሱን በመመልከት፥ የእርሱን አሠራር በመቅዳት) ከክርስቶስ ጋር ጊዜ ልናሳልፍ ይገባናል።

ከክርስቶስ ጋር ጊዜ ስታሳልፉ በአራት የተለዩ አቅጣጫዎች ይመራችኋል። እግዚአብሔርን እንድትወዱ፥ ከአማኞች ጋር አንድ እንድትሆኑ፥ ዓለምን እንድታገለግሉ እና ወንጌሉን እንድታስተላልፉ ይመራችኋል። አጠቃላዩ የክርስትና ሕይወት ከዚህ የክርስቶስ ፍለጋ እየወጣ የሚፈስ ነው።

### እግዚአብሔርን መውደድ ማለት

- ከእግዚአብሔር ጋር ባለን የግል ግንኙነት መደሰት ነው
- በቃሉ አማካኝነት እርሱን ወደ ማወቅ መድረስ ነው
- በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር ነው
- ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ማሳለፍ ነው
- በሕይወታችን እርሱን ማምለክ ነው
- በመጀመሪያው እና በታላቁ ትእዛዝ መሠረት መኖር ነው። (ማቴዎስ 22፥37–38)

## ከአማኞች ጋር አንድ መሆን ማለት

- ከሌሎች አማኞ ጋር ጠንካራ ግንኙነት በመለማማድ መደሰት እና ማዳበር ነው።
- ሕይወታችንን በወንጌል ተልዕኮ፥ በጸሎት፥ በአገልግት፥ በራእይ፥ በፍቅር፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፥ ወዘተ አንድ ማድረግ ነው።
- ክርስትና በማኅበር ከሌሎች አማኞች ጋር የሚኖሩት እንደሆነ መረዳት ነው።
- እርስ በእርሳችን መዋደድ እና ማገልገል ነው።

## ዓለምን ማገልገል ማለት

- በቃላት ብቻ ሳይሆን በተግባር ለሰዎች ፍቅር ማሳየት ነው
- ለዓለማችን እና ለሃብቷ መልካም ባለ አደራ መሆን ነው
- ሌሎችን የማገልገልን የክርስቶስ ምሳሌ መከተል ነው
- ሕይወታችንን በሰዎች ላይ፥ በቤተሰቦች ላይ፥ በማኅበረሰብ ላይ እና በሕዝቦች ላይ ማፍሰስ ነው።


## ወንጌሉን ማስተላለፍ ማለት

- የመንግሥቱን ወንጌል ማካፈል ነው።
- የክርስቶስን ትምህርቶች ለሌሎች ማስተላለፍ ነው። (". . . ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲፈጽሙ እያስተማራችኋቸው...")
- ሌሎችን በእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ ውስጥ እንዲሳተፉ መጋበዝ ነው።

የቤተ ክርስቲያን ሕንጻዎችን፥ የገንዘብ በጀቶችን፥ እና መርሐ ግብሮችን ወደ ጎን ካደረጋችሁ ደቀ መዝሙር መሆን ማለት ክርስቶስን መፈለግ ነው። ክርስቶስን ስንፈልግ እርሱ እግዚአብሔርን እንድንወድ፥ ከአማኞች ጋር አንድ እንድንሆን፥ ዓለምን እንድናገለግል እና ወንጌሉን እንድናስተላልፍ ይመራናል።

የእያንዳንዱ ሰው ጉዞ በጥቂቱ የተለያየ ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን የደቀ መዝሙር አካሄድ በተመሳሳይ አቅጣጫ ነው። ክርስቶስ እንድንወድ፥ እንድንተባበር፥ እንድናገለግል እና እንድናስተላልፍ ይመራናል።

አሁን የተመለከታችሁት ሂደት እንደ አንድ መንፈሳዊ ኮምፓስ ሆኖ ሊያገለግላችሁ ይችላል። የሕይወታችሁ ጉዞ በክርስቶስ ወደ መብሰል እያደገ መሆኑን ለማረጋገጥ ከፈለጋችሁ እነዚህን እውነታዎች ወደ ሕይወታችሁ መልሱ እና እግዚአብሔር የጎደለውን እንዲገልጥላችሁ ጠይቁት። እግዚአብሔርን መውደድ የግድ "መንፈሳዊ የሰሜን ዋልታችን" ሆኖ ሊጸና ይገባዋል። እኛ እግዚአብሔርን በመውደድ ላይ ስናተኩር ሌሎቹ በመንፈሳዊ ኮምፓሳችን ላይ ያሉት አቅጣጫዎች በሚገባ እያመለከቱ ይሠራሉ።




በሕይወታችሁ ላይ ይህንን መንፈሳዊ ኮምፓስ ስታደርጉ አንዳንድ የአቅጣጫ ማስተካከያዎችን የማድረግ አስፈላጊነትን ልትመለከቱ ትችላላችሁ። ምናልባት ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ እያሳለፋችሁ እንዳልሆነ ልታዩ ትችላላችሁ። ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት እያደረጋችሁ እንዳልሆነ ወይም ዓለምን እያገለገላችሁ እንዳልሆነ ወይም እምነታችሁን እያካፈላችሁ እንዳልሆነ ልታስተውሉ ትችላላችሁ። አንዴ ምን እንደ ጎደለ ካወቃችሁ እግዚአብሔር ያንን ክፍል በእናንተ ውስጥ እርሱ ራሱ እንዲኖረው ጠይቁት።

በተጠቀሱት አራት አቅጣጫዎች መሠረት የትኞቹ አቅጣጫዎች በእናንተ ሕይወት ተጓድለዋል? በዚህ ጉዳይ ላይ እንዲደግፏችሁና እንዲሳተፉ እነ ማንን ልታነጋግሩ ትችላላችሁ?

ደቀ መዛሙርት እንድንሆን እና ደቀ መዛሙርትን እንድናፈራ ተጠርተናል። ከማን ልትማሩ ትችላላችሁ (ስማቸውን ዘርዝሩ) ለማን ልታካፍሉ ትችላላችሁ (ስማቸውን ዘርዝሩ)?

# 5ኛ ቀን፥ መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ላጠና እችላለሁ?

የሚከተለው ዓረፍተ ነገር በጌዴዎናውያን መጽሐፍ ቅዱሶች ሽፋን ውስጠኛ ገጽ ይገኛል። ጸሐፊው አይታወቅም ነገር ግን ጭምቅ አሳቡ ጠሊቅ እና ወቅታዊ ነው። መጽሐፍ ተብሎ እየተገለጸ ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው።

> ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን አእምሮ፥ ሰው ያለበትን ሁኔታ፥ የደህንነትን መንገድ፥ የኃጢአተኞችን መጨረሻ እና የአማኞን ደስታ የያዘ ነው። አስተምህሮዎቹ የተቀደሱ ናቸው፥ ሃሳቦቹ ገዢ ናቸው፥ ታሪኮቹ እውነት ሲሆኑ ውሳኔዎቹም ፍጹም ናቸው። ጠቢብ እንድትሆኑ አንብቡት፥ እንድትድኑ እመኑት ብሎም እንድትቀደሱ ተግባራዊ አድርጉት።
>
> መንገዴን እንዲመራኝ ብርሃንን፥ እንዲያጸናኝ ምግብን እና ደስ ሊያሰኘን መጽናኛን ይዟል። ይህ መጽሐፍ የተጓዦች ካርታ ነው፥ የመናኞች በትር፥ የፓይለቶች ኮምፓስ፥ የወታደሮች ሰይፍ እና የክርስቲያኖች ባህርይን የያዘ ነው።
>
> እዚህ ገነት እንደገና መጥቷል፤ መንግሥተ ሰማይ ተከፍቷል፤ ብሎም የገሃነም ደጆች ተገልጠዋል። ክርስቶስ የዚህ ዋናውና ታላቁ አካል ነው። የኔ መልካምነት ዓላማው ሲሆን የእግዚአብሔር ክብር ደግሞ ፍጻሜው ነው። ትዝታን ሊሞላ፥ ልብን ሊገዛ እና እግርን ሊመራ ይገባዋል።
>
> በዝግታ፥ በቋሚነት እና በጸሎት መንፈስ አንብቡት።
>
> በሕይወት እያለሁ ተሰጠኝ፤ በፍርድ ቀን ይከፈታል፤ እናም ለዘላለም ይታወሳል። እጅግ የላቀውን ኃላፊነት ይዟል፤ የታላቁን ልፋትም ዋጋ ይሰጣል፤ ከተቀደሱት ነገሮቹ የጣሉትንም ይፈርድባቸዋል።

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንነት መግለጫ ጉልበታም እና እውነት ነው። ይሁንና እኛ በጣም ቀላል የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጉም መስጠት እንሻለን።

> መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እራሱን ለሰው ልጆች የገለጠበት ግልጠት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ለእኛ እንደ ደቀ መዝሙርነታችን መጠን እያደግን ለመሄድ እጅግ ወሳኝ ነው። አስተምህሮአዊ እምነቶች እና የግል እርግጠኛነቶች በሙሉ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነቶች ሊመዘኑ ይገባቸዋል። የሚከተሉት ጥያቄዎች ቃሉን በማጥናት የሚመለሱ ናቸው።

- የቱ እውነት እንደሆነ እንዴት አውቃሁ?
- እግዚአብሔር ከእኔ የሚጠብቀውን እንዴት አውቃለሁ?
- እግዚአብሔርን እንዴት አውቃለሁ?
- እምነቶቼ እውነት መሆናቸውን እንዴት አውቃለሁ?
- ቤተሰቤን እንዴት መምራት እንዳብኝ እንዴት አውቃለሁ?
- እንደ ደቀመዝሙር እንዴት መኳዝ እንደሚገባኝ እንዴት ልማር እችላለሁ?

እንደነዚህ ዓይነቶቹ ጥያቄዎች ሁሉ የሚመለሱት መጽሐፍ ቅዱን ስናጠና ነው። 2ጢሞ. 3፥15-17 "ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል። የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፥ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።" ይላል።

## መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበት ወቅት በአእምሮአችን ልንይዝ የሚገባን በርካታ ቁልፍ አሳቦች አሉ።

### 1. መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው።

- “የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ …” (2 ጢሞ. 3፥16ሀ)
- በይዘቱ በእስትንፋስ መለኮት የሆነ፤ በበኩራት ጽሑፎቹ ስሑትነት የሌለበት፤ በአስተምህሮው የማይወድቅ ነው።
    - o እስትንፋሰ መለኮት የሆነ፥ እግዚአብሔር እፍ ያለበት (በጸሐፊዎቹ በኩል)፤
    - o ስሑትነት የሌለበት፤ የማይሳሳት፥ ስሕተት የማይገኝበት።
    - o የማይወድቅ፤ የማይሻሻል፤ የማይለዋወጥ፤ አስተማማኝ፤ ሊሳሳት የማይችል።

**2. መንፈስ ቅዱስ መረዳትን ያስችለናል።**

*“ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፥ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፥ የሚመጣውንም ይነግራችኋል።”* (ዮሐ. 16፥13)።

እንደ ክርስቲያን መንፈስ ቅዱስ ከእናንተ ጋር ብቻ አይደለም ነገር ግን በእናንተ ውስጥ ነው። (ዮሐ. 14፥17)።

**3. መጽሐፍ ቅዱስን የሚተረጉመው መጽሐፍ ቅዱስ ነው።**

*“ይህን በመጀመሪያ እወቁ፥ በመጽሐፍ ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም አልተፈቀደም፥ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።”* (2ጴጥ. 1፥20–21)።

አንድ ምንባብ ካልገባችሁ ቃሉ ጥያቄያችሁን እንዲመልስ ፍቀዱለት።

**4. ዐውዱ ትርጉሙን ይፈታል።**

እንደሚገባ አንድን ምንባብ ለመተርጎም፥ እንዲህ ልናውቅ ይገባል፤

- ደራሲ፥ መጽሐፉን ማን ጻፈው?
- ተደራሲ፥ መጽሐፉ ለማን ነው የተጻፈው?
- መቼት፥ በተደራሲዎቹ እና በጸሐፊው መካከል ምን እየተካሄደ ነበር?
- ዓላማ፥ መጽሐፉ ለምንድን ነው የተጻፈው?
- ዘውጉ፥ የአጻጻፉ አይነት ምንድን ነው? (ታሪካዊ ትረካ፥ ግጥም፥ ቅኔያዊ/ ኪነ ጥበባዊ፥ ትንቢት፥ አቡቀለምሲሳዊ የምጽአት ጽሑፍ፥ ደብዳቤዎች፥ ወዘተ።)

(ከእነዚህ መረጃዎች ብዙዎቹ ወይም ሁሉም በመጽሐፍ ቅዱስ ማጥኛ መጽሐፍ በእያንዳንዱ መጽሐፍ መጀመሪያ ላይ ይገኛሉ።)

## 5. አንድ ትርጉም እና በርካታ ተዛምዶዎች ወይም ግንዛቤዎች ይኖራሉ።

ትርጓሜው መጀመሪያ ለተጻፈበት ዐውድ የተለየ መሆን አለበት። አንድ ጊዜ የመጀመሪያው ጸሐፊ ለመጀመሪያዎቹ ተደራሲዎች ሊናገር ያሰበውን ካወቅን በኋላ እውነታዎቹን ከራሳችን ሕይወት ጋር ማዛመድ መጀመር አንችላለን።

## 6. ግቡ እርሱን ለማወቅ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት የመጨረሻ ግብ እውቀት አይደለም፥ መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት የመጨረሻ ግብ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ጊዜን እና ቋሚነትን ወይም አለማቋረጥን ይጠይቃል። ሁሉንም ነገር በአንድ ጊዜ ልትረዱ አትችሉም። ጥያቄዎቻችሁን ጻፉ እና ለመረዳት ጸልዩ። ከዚያም እንዲመልስላችሁ ለእግዚአብሔር ጊዜ ስጡት።

መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ ዛሬ ጀምሩ። የት ጋ መጀመር እንዳለባችሁ ካላወቃችሁ በዮሐንስ ወንጌል ጀምሩ።

ተጨማሪ ማስታወሻዎች፤

## 6ኛ ቀን፥ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ለምን ይገባኛል?

አንድ ሰው ''እግዚአብሔርን ወዳለሁ ነገር ግን ያንን ለማስመስከር ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ የለብኝም።" ሲል ሰምታችሁ ታውቁ ይሆናል። ትክክል ናቸው! ኢየሱስ "በየእሁዱ ቤተ ክርስቲያን ከሄዳችሁ ይሄ እኔን እንደምትወዱ የምታውቁበት መንገድ ነው።" አላለም።

ወደ ቤተ ክርስቲያን መሄድ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር ለማሳየት ሲባል ግድ ካልሆነ ታዲያ የቤተ ክርስቲያን አስፈላጊነት ምንድን ነው ?

መልሱ ሊያስደንቃችሁ ይችል ይሆናል። በክርስቶስ የማደጋችሁ አንዱ ክፍል የሚከሰተው ከሌሎች አማኞች ጋር በኅብረት ስትሆኑ ብቻ ነው። ይህም ለብቻ ታላቅ የእግር ኳስ ተጫዋች ለመሆን ከሚደረግ ጥረት ጋር እኩል ነው። በግላችሁ በርካታ ነገሮችን ብቻ ልትማሩ ትችላላችሁ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ግን ስፖርቱን በሚገባ ለመረዳት እና ችሎታችሁን ለማዳበር በቡድን ውስጥ መግባት ያስፈልጋችኋል።

ክርስትና የቡድን ስፖርት ነው። በእርግጠኝነት እውነቶችን ለብቻችን ልንማር እንችላለን፥ ሆኖም እውነቶቹ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚገለጡት ከሌሎች አማኞች ጋር ስንሆን ነው። በአራተኛው ቀን እንደተማራችሁት ደቀ መዝሙር የመሆን አንዱ ክፍል ከሌሎች አማኞች ጋር አንድ መሆን ነው። አግዚአብሔር እንድትሆኑ የፈጠራችሁን ሙሉ ለሙሉ ለመሆን እንድትችሉ ከፈለጋችሁ ያ የሚሆነው በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ማኅበረሰብ ውስጥ ነው።

ሳምንታዊ የአምልኮ መርሐ ግብሮቻችን ለመንፈሳዊ ዕድገታችን በብዙ እንገዶች አስተዋጽዖ ያደርጋሉ። ዋናዎቹ እነዚህ ናቸው፤

### 1. ከሌሎች አማኞች ጋር የመንገናኝበት ስፍራ ነው።

*"ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፥ ያላቸውንም ሁሉ አንድነት አደረጉ። መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር። በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ ምግባቸውን ይመገቡ ነበር። . . ."* (ሐዋ. 2፥44–46)።

## 2. አግዚአብሔርን የማምለኪያ ስፍራ ነው።

“ሃሌ ሉያ። እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት በኃይሉ ጠፈር አመስግኑ!” (መዝ. 150፥1)።

## 3. የቃሉን ትምህርት መስሚያ ስፍራ ነው።

“በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።” (ሐዋ. 2፥42)።

## 4. ሌሎችን የማገልገያ ስፍራ ነው።

“ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ስጦታ እንደ ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርስ በርሳችሁ አገልግሉ፥” (1ጴጥ. 4፥10)።

## 5. የብርታት ማግኛ ስፍራ ነው።

“በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፥ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።” (ዕብ. 10፥25)።

## 6. የመፈተኛ፥ የመፈተሻ፥ ተግዳሮትን የመቀበያ ስፍራ ነው።

“ብረት ብረትን ይስለዋል፥ ሰውም ባልንጀራውን ይስላል።” (ምሳሌ 27፥17)።

በኤፌ. 4 ጳውሎስ እንዴት እያንዳንዱ ሰው በክርስቶስ አካል ውስጥ ጠቃሚ እና ተፈላጊ እንደሆነ ያሳያል። *"ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።"* (ኤፌ. 4፥16)። እያንዳንዱ ክርስቲያን ለቤተ ክርስቲያ የሚያበረክተው ነገር አለው። እኛ ለመሳተፍ፥ ለማገልገል እና በጋራ ለመሥራት ፈቃደኛ ስንሆን አካል ሁሉ ጤናማ እና የሚያድግ እንዲሁም በፍቅር የተሞላ ይሆናል።

ጳውሎስ በቆሮንቶስ ላሉት አማኞች ሲናገር፥ አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ጥገኛ እንደሆኑ ይነግራቸዋል። *"ነገር ግን ብልቶች እርስ በርሳቸው በትክክል ይተሳሰቡ ዘንድ እንጂ በአካል መለያየት እንዳይሆን፥ ለጎደለው ብልት የሚበልጥ ክብር እየሰጠ እግዚአብሔር አካልን አገጣጠመው።"* (1ቆሮ. 12፥25)። ከሌሎች አማኞች ጋር መሆን መልካም ብቻ አይደለም፥ የግድ አስፈላጊ ነው። አንዳችን ለአንዳችን እናስፈልጋለን። **በክርስቶስ ያለን ዕድገት አንዱ ክፍል የሚከሰተው ከሌሎች አማኞች ጋር በኅብረት ስንሆን ብቻ ነው።**

## ለእናንተ ትክክለኛ የሆነ ቤተ ክርስቲያን/ ወይም የአማኞች ስብስብ እንዴት ልታገኙ ትችላችሁ?

- ምሪት ለማግኘት እና ለይቶ ለማወቅ ጸልዩ።
- የእግዚአብሔርን ቃል በታማኝነት የምታስተምር ቤተ ክርስቲያን ፈልጉ።
- ደቀ መዝሙር ስለማድረግ ቆራጥ አቋም ያለው ያለው ቤተ ክርስቲያን አግኙ (ይኸውም ባለፈው እንደተማርነው እግዚአብሔርን መውደድ፥ ከአማኞ ጋር አንድ መሆን፥ ዓለምን ማገልገል፥ ወንጌሉን ማስተላለፍ)።
- ስለራእያቸው፥ ተልእኮአቸው፥ እምነቶቻቸው፥ አገልግሎቶቻቸው፥ አመራራቸው፥ ወዘተ፥ ጥያቄዎችን ጠይቁ።
- ተሳተፉ።
- የሚስማማችሁ ከሆነ ቆዩ፥ የማይስማማችሁ ከሆነ የሚስማማችሁን ቤተ ክርስቲያን ፈልጉ።

የምትካፈሉባት ቤተ ክርስቲያን አላችሁን? ይህች ቤተ ክርስቲያን ከላይ ያነሣናቸውን መስፈርት ታሟላለችን? ካልሆነ የተጓደለው ምንድን ነው?

___

___

___

___

___

___

የምትካፈሉባት ቤተ ክርስቲያን ከሌላችሁ፥ ልትሄዱ እና ልትመረምሩ የምትፈቅዷቸውን የተለያዩ ቤተ ክርስቲያናት ጻፉ። እንዲሁም በዚህ ፍለጋችሁ ሊረዷችሁ ፈቃደኛ ሊሆኑ የሚችሉ የምታውቋቸውን ክርስቲያኖች ስማቸውን ጻፉ።

___

___

___

___

___

___

# 7ኛ ቀን፥ እንደ ክርስቲያን ለማደግ ምን ይጠበቅብኛል?

እንደ ክርስቲያን እንድታድጉ የሚረዱአችሁ የተለያዩ ዘርፎች አሉ። እነዚህን ዘርፎች መረዳት እና ለምን እንደምናደርጋቸው መረዳት አስፈላጊ ነው።

ዓላማውን ሳናውቅ በአንድ ተግባር ውስጥ መሳተፍ ከግንኙነት ይልቅ ወደ ሃይማኖት ይመራናል።

## 1. ተጠመቁ

መጠመቅ የመመሳሰል ወይም ወደ አካል ውስጥ የመግባት እና የመታዘዝ ተግባር ነው። በመጠመቅ የክርስቶስን ሕይወት፥ ሞት፥ መቀበር እና ትንሳኤ እውቅና እንሰጣለን፤ ወይም እነዚህን መታወቂያችን እናደርጋለን። (ማቴ. 3፥13–17)። ስንጠመቅ በታላቁ ተልዕኮ ውስጥ ያለውን የክርስቶስ ትምህርት እንታዘዛለን። (ማቴዎስ 28፥19–20፥ ማርቆስ 16፥16፥ የሐዋርያት ሥራ 2፥38)።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥምቀት ከደኅንነት በኋላ የሚሆን እና በማጥለቅ የሚካሄድ ነው። ጥምቀት ማንንም አያድንም፤ ጥምቀት በዳኑ ሰዎች አማካኝነት በሕዝብ ፊት እምነትን የመግለጽ ሥርዓት ነው።

## 2. በየቀኑ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜን አሳልፉ።

ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ የመውሰድን ጠቃሚነት በሁለተኛ፥ ሦስተኛ፥ እና አራተኛ ቀኖች አሳይተናል። የሕይወት ግብ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። የየዕለቱ ግብም ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ማሳለፍ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ለማሳለፍ የሚያገለግሉ በርካታ መንገዶች አሉ። ይሁንና ሁለቱ መሠረታዊ አቅጣጫዎች ጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ናቸው።

### ሀ. ጸሎት

ጸሎት በልባችሁ ያለውን ለእግዚአብሔር ማካፈል ሲሆን እንዲሁም እግዚአብሔር በእርሱ ዘንድ ያለውንም ለእናንተ ሲያካፍል ማድመጥ ነው። ጸሎትን በሁለት ወዳጆች መካከል እንደሚካሄድ ውይይት አድርጋችሁ አስቡት። አንድ ሰው ብቻ የሚናገር ከሆነ ያ ግለ ወግ ነው። ሁለቱም ሲያወሩ ያ ውይይት ነው።

የእግዚአብሔርን ድምጽ የሚሰማ ጆሮ ለማዳበር ጊዜ ይወስዳል። በጸሎት ውስጥ ያለው የእግዚአብሔር ድምጽ መቼም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካለው የእግዚአብሔር ድምጽ ጋር አይቃረንም። እግዚአብሔር አብዛኛውን ጊዜ ጸሎታችንን፥ ጥያቄያችንን ይመልሳል ብሎም በቃሉ አማካኝነት አሳቡን ይገልጻል። ጸሎት እና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አጅ ለእጅ ተያይዘው የሚሄዱ ናቸው።

ለ. ቃሉን አጥኑ በቃላችሁም ያዙት

አስቀድመን መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ማጥናት እንደሚቻል መሠረታዊ አሳቦችን አይተናል፤ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ለምን እናጠናለን? መጽሐፍ ቅዱስን የእግዚአብሔርን የልቡን አሳብ፥ የእርሱን ምሪት፥ የእርሱን አቅጣጫ ወዘተ፥ ለማወቅ እናጠናለን። መጽሐፍ ቅዱ ኅያው ነው (ዕብ. 4፥12)። መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ እርሱንም ለሕዝቡ በቀጥታ ለመናገር ይጠቀምበታል።

የትጋ ትጀምራችሁ? የሚከተሉት የልዩ ልዩ አማራጭ ጥቆማዎች ናቸው።

- የዮሐንስን ወንጌል አንብቡ (በቀን አንድ ምዕራፍ)። ሁለት ጥያቄዎችን ጠይቁ። ኢየሱስ ማነው? የኢየሱስ ተከታይ መሆን ማለት ምን ማለት ነው? መልሶቹን ከማጣቀሻዎች ጋር ጻፉ።
- መጽሐፈ ምሳሌን አንብቡ (በቀን አንድ ምዕራፍ ብታነብቡ በወር ትጨርሱታላችሁ)።
- አዲስ ኪዳንን አንብቡ (ከማቴዎስ እስከ ራእይ)። በቀን ሦስት ምዕራፍ ካነበባችሁ፥ ሙሉውን አዲስ ኪዳን ለመጨረስ ሦስት ወር አካባቢ ይፈጅባችኋል።
- ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ አንብቡ (ከዘፍጥረት እስከ ራእይ)። መጽሐፍ ቅዱስን በዓመት ለማንበብ በርካታ ዕቅዶች አሉ። ዕቅዱን ከኢንተርኔት ማውረድ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ዓመት የሚል መጽሐፍ ቅዱስ መግዛት ትችላላችሁ። መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ዓመት የሚለው መጽሐፍ በየዕለቱ ከብሉይ ኪዳን፥ ከአዲስ ኪዳን፥ ከምሳሌ እና መዝሙር መጽሐፎች የሚነበብ እየሰጠ በዓመት ውስጥ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ያስጨርሳችኋል።

ለእናንተ ልዩ ትርጉም ያላቸው ቁልፍ ጥቅሶችን ስታገኙ፥ እነዚያን በቃላችሁ አጥንታችሁ ለመያዝ ጊዜን ውሰዱ። እግዚአብሔር አብዛኛውን ጊዜ በጸሎት ሲገናኘን በቃላችን ያጠናናቸውን ጥቅሶች ወደ እኛ ያመጣል።

## 3. ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ተባበሩ።

በስድስተኛው ቀን ላይ የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጠቀሜታን ተወያይተናል። እንደ አንድ የክርስቶስ ተከታይ ለማደግ ከሌሎች አማኞች ጋር  በኅብረት ውስጥ ልትሆኑ ይገባል። የሚከተሉት አንዳንድ የተለመዱ አካሄዶች ናቸው።

ሀ. የጋራ አምልኮ

የጋራ አምልኮ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር እውቅና ስለመስጠት እና ስለመናገር ተብሎ የሚደረግ ነው። እርሱ ማን እንደሆነ እና በቃሉ አማካኝነት ምን እንዳደረገ እውቅና እንሰጣለን። ፍቅራችንን በዝማሬ፥ በጸሎት፥ በማስተማር፥ እና በንግግር እንገልጣለን።

ለ. የአነስተኛ ቡድን ወይም የሰንበት ትምህርት ክፍል አባል ሁኑ

አነስተኛ ቡድኖች ወዳጅነትን እንድታዳብሩ የሚያግዙ እና ጥያቄዎችን ለመጠየቅ ዕድል የሚሰጡ ናቸው። አነስተኛ ቡድኖች በክርስቶስ የሆነ እድገታችሁን ያቀጣጥላል፤ ያፋጥናል።

ሐ. ለእግዚአብሔር ሥራ ስጡ

መስጠት የአምልኮ እና የእምነት ተግባር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የሁሉ ባለቤት እንደሆነ እና ከፊሉን ለኛ ኃላፊነት ሰጥቶ እንዳካፈለን ይነግረናል። እግዚአብሔር አስራት (10%) ለእርሱ መልሰን እንድንሰጥ ይነግረናል። አንድ ክርስቲያን ለእግዚአብሔር መልሶ አስራት ሲሰጥ ያ የመታዘዝ እና የእምነት ተግባር ነው። በዚህም የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ይታዘዛሉ፤ እናም ለራሳቸው ከሚይዙት ከ100% ይልቅ በቀረው 90% እግዚአብሔር የበለጠ እንደሚያደርግ ይታመናሉ።

መ. ተሳተፉ

ከመጋቢያችሁ ጋር ተነጋገሩ፤ የራሳችሁን መንፈሳዊ ስጦታ(ዎች) አግኙ፤ የአገልግሎት ቦታ ፈልጉ፤ ሕዝቡን እወቁ፤ ተሳተፉ። ክርስቲያኖች ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሲሆኑ ለመያያዝ ዕድሎችን ያገኛሉ። ሌሎች እስኪጋብዟችሁ ከጠበቃችሁ ረጅም ጊዜ ትጠብቁ ይሆናል። እራሳችሁ አነሳሽ ሁኑ።

በእነዚህ ሁሉ ደረጃዎች ግቡን አስቡ። ግቡ ከተሰጡ ግዴታዎች የተነሣ ሃይማኖታዊ ተግባሮችን መፈጸም አይደለም። ግቡ እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናታችሁ፥ ጸሎታችሁ፥ እና የቤተ ክርስቲያን ተሳትፎአችሁ ከእግዚአብሔር ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዲኖራችሁ ይምሩዋችሁ።

ተጨማሪ ማስታወሻዎች፤

# መደምደሚያ

ባለፉት ሰባት ቀናት በክርስቶስ የሆነውን አዲስ ሕይወታችሁ መሠረታዊ አሳቦች አይተናል። ይህ ማለት ታዲያ ክርስትናን በሙሉ ሸፍነናል ለማለት የተነገረ አይደለም። የሥነ መለኮትን፥ የክርስቶስ ሕይወትን፥ በክርስቶስ ያለንን ስፍራ እና ሀብት ወዘተ፥ ገና ጫር እንኳ አላደረግንም። ሆኖም የሚከተሉትን ተመልክተናል፤

- በክርስቶስ ያላችሁን ማንነት
- የዘላለም ሕይወትን
- የክርስቲያን ሕይወት ግቦችን
- የክርስቶ ደቀ መዝሙር ማለት ምን ማለት እንደሆነ
- መጽሐፍ ቅዱስን እንዴት ማጥናት እንደሚቻል
- የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ጠቀሜታን
- በክርስቶስ ለማደግ የሚያስፈልጉ ደረጃዎችን

**እነዚህ ትምህርቶች ሁሉ በአንድ ሳምንት ውስጥ ተሰጥተዋል፤ ነገር ግን በሕይወት ዘመን ሁሉ ሊተገበሩ ይገባቸዋል።**

የበለጠ መጽሐፍ ቅዱን ባጠናችሁ፥ የጋራ አምልኮ በተካፈላችሁ እና ከአማኞች ጋር አንድ በሆናችሁ ቁጥር የበለጠ እግዚአብሔር ጥልቀቱንና ዝርዝሩን እየሞላ ይመጣል።

የክርስትና ሕይወት አጭር ሩጫ እንዳልሆነ ለማስታወስ ሞክሩ፤ ማራቶን ነው። መሠረታዊ ነገሮቹን በሚገባ ተማሩ እና በጊዜ ሂደት ወደ መብሰል ታድጋላችሁ። የበለጠ ርቀት ስትሄዱ የሚከተለውን እውነታ ጠቃሚነትን የበለጠ ታያላችሁ :

እግዚአብሔር በእናንተ ሕይወት ውስጥ እና በእናንተ ሕይወት አማካኝነት ሊሠራ የሚሻውን ሁሉ ከክርስቶስ ጋር ካላችሁ የተትረፈረፈ ግንኙነት በመነሣት ይፈጽመዋል። ደግሞም፥ ጥቂት ነገሮችን ብቻ አይደለም፤ ሁሉንም ነው! - ሁሉንም ነገሮች።

እርሱን መፈለጋችሁን በቀጠላችሁት ልክ አግዚአብሔር ይባርካችሁ!

ለሳምንቱ ትኩረታችን የነበረው በክርስቶስ የሆነውን አዲስ ሕይወታችሁን መሠረታዊ ነጥቦች ስለማካፈል እና ከእግዚአብሔር ጋር የተነቃቃ ግንኙነት ለማዳበር በትክክለኛ መንገድ ላይ ማስቀመጥ ነበር።

እነዚህን መርሆች ለተጨማሪ ወር ለማስቀጠል መከተል የሚለውን ቅጂ አግኙ። መከተል በፒዲኤፍ መልክ ከwww.thisistheGospel.com ይገኛል። የታተመ የመከተልን ቅጂ በሚከተለው ኢሜይል በመጻፍ ይገኛል። info@lifebaptistchurch.com



# የክርስቶስ ሕይወት መርጃዎች / መገልገያዎች

ኅብረት ስላላበት ኑሮ እና የክርስቶስ ሕይወት አይኖቻችሁ ከተከፈቱ በኋላ ወደ ሞተ ሃይማኖት መመለስ የለም። ጥያቄው "የበለጠ ለመማር ወደ የት መሄድ ይኖርብኛል?" የሚል ይሆናል።

ጠንካራ የኅበረት አትኩሮት ያላቸውን መጻሕፍት ዝርዝርም በመጨረሻው ገጽ አካትተናል። ከእነዚህ መጻሕፍት እንዳንዶቹ ከሕትመት ውጪ ሆነዋል፤ ነገር ግን በአሮጌ የመጻሕፍት መደብሮች ሊገኙ ይችላሉ። ከእነዚህ ደራሲያን የተወሰዱ ቁልፍ አሳቦች ወንጌሉ ይህ ነው (This is the Gospel) በሚሉት መገልገያዎ ውስጥ ቀርበዋል።

አንዳንዶቹ መጻሕፍት የዚህ የጥሞና መምሪያ አዘጋጆች ያልተቀበሏቸውን ትምህርቶች ያቀርባሉ። ለምሳሌ ስታንፈርድ አማኞች ኃጢአተኛ ተፈጥሮንም ሆነ አዲሱን ፍጥረት ሁለቱንም (በአንድ ጊዜ) ይኖሯቸዋል ብሎ ያስተምራል። እኛ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት አንስማማም። ማክቬይ፥ ፎስተር እና ጆርጅ በየራሳቸው መጽሐፍ ጠንካራ የተቃውሞ ምላሽን ያቀርባሉ። እኛ እነዚህን መጻሕፍት በዝርዝሩ ውስጥ ያካተትናቸው በሌሎች የኅብረት ጉዳዮች ላይ የተረጋገጡ ምልከታዎችን ስለሚያቀርቡ ነው። ስታንፈርድ እግዚአብሔር አማኝን ወደ እውነት የሚያደርስበት ሂደት ዙሪያ ከሚጽፉት ጸሐፍት መካከል ከታላላቆቹ አንዱ ነው። ጥቂት ልዩነቶች መኖራቸው እንግዳ ቢሆንም የበሰለ አማኝ በቅዱስ ቃሉ ብርሃን ስሕተትን ለመለየት ችግር አይኖርበትም።

እነዚህን መጻሕፍት ስታነቡ፥ በኅብረት ላይ ቁልፍ የሆኑ ጽንሰ አሳቦችን ለማግኘት ሞክሩ። ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ፥ በእርሱ መኖር፥ ሕይወት ከማድረግ ይልቅ መሆን፥ እግዚአብሔርን ማወቅ፥ ከክርስቶስ ጋር መቆራኘት፥ የእግዚአብሔር በእናንተ ውስጥ መኖር፥ ዐውዳዊ እውነት ወይም በክርስቶስ የሆነ እውነት የሚሉ ሃረጎችን ማስታወሻ ያዙ። እነዚህ ሐረጎች ወደ ተትረፈረፈ ኅብረት ይመሯችኋል።

## የተጠቆሙ መገልገያዎች ዝርዝር

- *Grace Walk* by Steve McVey
- *The Complete Green Letters* by Miles Stanford
- *Because We Love Him* by Clyde Cranford
- *Transformed Into His Image* by David Foster
- *Grace Amazing* by Steve McVey
- *Complete in Christ* by Bob George
- *The Explicit Gospel* by Matt Chandler
- *The Rest of the Gospel* by Stone and Gregory
- *Laws for Liberated Living* by Manley Beasley
- *Classic Christianity* by Bob George
- *Calvary Road* by Roy Hession
- *The Indwelling Life of Christ* by W. Ian Thomas
- *Truefaced* by Thrall, McNicol Lynch
- *Renovation of the Heart* by Dallas Willard
- *Alive By His Life* by Manley Beasley
- *The Law of Liberty in the Spiritual Life* by Evan Hopkins
- *Born Crucified* by L.E. Maxwell
- *Grace Rules* by Steve McVey
- *Falling for God* by Gary Moon
- *Not I But Christ* by Stephen Olford
- *Gospel* by J. D. Greear
- *Jesus + Nothing = Everything* by Tullian Tchividjian
- *Jesus Changes Everything* by Bob George
- *To Live is Christ To Die is Gain* by Matt Chandler

## ጥያቄዎች ካሏችሁ በዚህ አድራሻ እባካችሁን አግኙን፤

info@lifebaptistchurch.com

ግንኙነት